**የልብ መዛል/የተስፋ መቁረጥ ምክንያቶች** (ዕብ 12፡1-3፤ መዝ 77፡1-3-6-10)

ዕብ 1፡1፣ በፊታችን ያለውን የተወሰነልን/የተመደበልን ሩጫ እንሩጥ ይለናል፡፡ ይሄ ማለት በክርስትና ሕይወታችን ለያንዳንዳችን የተመደበ ሩጫ እንዳለ ያሳያል፡፡ ጌታን በእምነት ከተቀበልንበት ጊዜ ጀምሮ ምድራዊ ኑሮዋችን እስከ ሚፈጸምበት ዕለት ድረስ ባለው ጊዜ እግዚአብሔር እንድናከናውነውና እኛም በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድንደርስበት የተመደበልን ግብ የማሳካት ሩጫ አለ፡-

- ከዚህ በፊት በነበረው ዕድሜያችን የኖርነው የክርስትና ሕይወት አለ፡፡ እስካሁን ያለፍንበትን የክርስትና ሕይወት ስናስብ ስንት አግባባዊ ያልሆኑ ተግባራት በመፈጸማችን ዛሬ ይቆጨናል? ጊዜውን ወደኋላ ቀልብሰን ያበላሸነውን ነገር እያስተካከልን የመምጣት ዕድል ብናገኝ ብለን እናስብ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ግን እርሱን አይፈልገውም፡፡
- እርሱ የሚፈልገው ካለፈው የራሳችን ሕይወትና እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን የእምነት ምስክሮች ተምረን አንዳንዶቹ በወደቁበት ነገር እኛም እንዳንወድቅ፣ እነርሱ በእምነት በመጽናት የበረቱበትን መልካም ምሳሌነት ያለውን ተግባራቸው እኛም ተጠቅመንበት ከዛሬ ጀምሮ በቀረው ዕድሜያችን እስከ ፍጻሜው በአግባቡ ተጉዘን/ሮጠን መድረስ ያለብን አምላካችን ወዳየልን በጽድቅ ሕይወት የማደግ ግብ ላይ እንድንደርስ ነው፡፡ ይህን ብናደርግ ያመለጠን ብዙ ነገር እግዚአብሔር እጃችን እንዲገባ ያደርገዋል፡፡

ከፊታችን ያለው ሩጫ ስኬታማ እንዲሆንና ዝለን/ተስፋ ቆርጠን እንዳንወድቅ/ከሩጫው መስመር እንዳንወጣ ሩጫውን ከመጀመራችን በፊት ማስወገድና ራሳችንን ማመቻቸት የሚያስፈልጉን ነገሮች አሉ፡፡ እነርሱም፡ -

1. <u>አላስፈላጊ ሸክም የሚሆኑብን (ወደኋላ የሚጎትቱ)</u> **ነገሮች ሁሉ ማስወገድ፡፡** ለተመደበልን ሩጫ የማያስፈልግ ሸክም ተሸክሞ መሮጥ ባጭር ጊዜ ውስጥ ጉልበትን ስለሚያደክም በተገቢው ጊዜ ከፍጻሜ መድረስ አያስችልም፡፡

አንድ በሩጫ እስፖርት የሚወዳደር ሰው፣ ሩጫዬን ሊያጓትቱብኝ ይችላሉ የሚላቸው ማናቸውም ነገሮች (የራሱን ሰውነት ከመጠን ያለፈ ክብደት ጭምር) ሁሉ እንደ ሚያስወግድ አማኝም የእምነት ጉዞውን የመንፈሳዊ አገልግሎቱ/ሕይወቱ ትጋት የሚያደናቅፉ/የሚያጓትቱ ነገሮች ማስወገድ አለበት። ዓለማዊ ምኞት (የምድራዊ ኑሮ ድሎት፣ የራስ ክብር) የማሳካት ዕቅድ፣ የሰው ይሉኝታ፣ ባልተገባ ማህበራዊ ኑሮ መጠላለፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ፣ መንፈሳዊ ተግባራትን ለማከናወን ጊዜ የሚበሉ አስፈላጊ ያልሆኑ ነገሮችን ማንበብ፣ ቪዲዮዎችን/ጌሞችን መመልከት/መጫወት …ወዘተ ማስወገድ የስፈልጋል።

ወደ ኋላ የሚጎትት ነገር፣ ካሉበት ደረጃ ወደፊት/ወደላይ እልፍ ማለትን የሚከለክል ብቻ ሳይሆን ቀድሞ ከነበሩበት ብዙ እርምጃ ወደታች/ወደ ኋላ የሚስብ ይሆናል፡፡ ለመንፈሳዊ ጉዞ/ሩጫ ሸክም የሚሆኑ/ወደ ኋላ የሚጎትቱ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህም ሀብት የማከማቸት ፍላጎት፤ የስልጣን ጥማት፤ የድሎት ኑሮ፤ የራስ ዝናና ከሰው

ዘንድ የሚገኝ ክብርን ከእግዘአብሔር ይልቅ መውደድና መፈለግ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ይሄ ብቻ ሳይሆን ስለምድራዊ ኑሮ በመጨነቅ ዋናው ትኩረት ምድራዊ ኑሮ ማመቻቸት ላይ ማድረግ መልካም ፍሬ በማፍራት በጽድቅ ህይወት ማደግን ይገታል/ያዳክማል፣ በመጨረሻም ዝሎ ወደ መውደቅ ሊያደርስ ይችላል፡፡ ጌታ ኢየሱስ በዘሪው ምሳሌ እሾህ አነቀው መልካም ፍሬም ማፍራት አልቻለም በማለት በሌላ መልኩ ገልጾታል፡፡

እነዚህ ምድራዊ ነገሮች በጣም ብዙ ሰው ከእግዚአብሔር ይልቅ ይፈልጋቸዋል፡፡ ሆኖም የሚፈልጋቸው ሁሉ ሲያገኛቸው አይታይም፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ እኔን ከልብ ፈልጉ ታገኙኛላችሁ፤ እንደ ሚለው ቃሉ ከልብ የሚፈልገው ሁሉ ያገኘዋል፡፡ "ከዚያም ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡፡ ከኋላዬ ሊመጣ (ከልብ ሊከተለኝ) የሚፈልግ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ፡፡ መስቀሉንም በየእለቱ ተሸክሞ ይከተለኝ፡፡" ሉቃ 9፡ 23

2. **በቀላሉ <u>ተብትቦ የሚይዘው</u> ኃጠአት ማስወገድ፡-** ኃጢአት ወይም እግዚአብሔርን አለመታዘዝ መንፈሳዊ ሕይወትን ተብትቦ (አስሮ) ስለሚይዝ በጠላት ፊት ራስን ለመከላከል እና ለማጥቃት ኃይል ያሳጣል፡፡ ከችካል ጋር ታስሮ የተያዘ እንስሳ ከአጥቂ አራዊት ራሱን መከላከል ወይም ማምለጥ እንደሚያሳጣው ያደርጋል፡፡ በውጫዊ ሰውነት ሲታይ ከእስር ቤት ውጪ ያለ በነጻነት የሚመላለስ ሊሆን/ሊመስል ይችላል፡፡ ግን ውስጣዊ ሰውነትና መንፈሳዊ ኃይልን እስረኛ ያደርጋል፡፡ ይህም
   - ነባርና ልማዳዊ በነበረ ኃጢአት መቀጠልና አዳዲስ ኃጢአትን መለማመድን፣
   - የስህተት አስተምህሮ መከተልን፤
   - በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነገር ያለበት ወግና ባህል መጠበቅን ስለሚያካትት መንፈሳዊ ኃይልና ህይወትን ማድከሙ የማይቀር ስለሆነ ሩጫ ከመጀመሩ በፊት ማስወገድ ያሻል፡፡

   ኃጢአትን ማስወገድ የሩጫው አካል ቢሆንም በሩጫው የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ በመደረግ መጀመር ያለበት ነው፡፡

3. **የተመደበልን ሩጫ መሮጥ፡-** ማቴ 7፡21-27 የሚጠበቅብን ሩጫ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን ቃሉን ሰምቶ/አጥንቶ ተግባር ላይ በማዋል መልካም ፍሬ እያፈሩ በቅድስና መኖርና የእግዚአብሔርን በሰጠው የጸጋ ስጦታ ማገልገል፤ አቅም የፈቀደውን ያህል ሚዛን ሳያዛቡ በትጋትና በቅድስና ለምድራዊ ኑሮ የሚያስፈልገውን ለማግኘት መስራት ያጠቃልላል፡፡ ሁለቱም ነገሮች የማይነጣጠሉ ከእያንዳንዱ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሚጠብቃቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሙሉ ጊዜውን እንዲሰጥ የተጠራ ሰው እንደ ጥሪው ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ መተግበር ለሕይወታችን

በእግዚአብሔር እጅ እንደ መያዝ ያህል የሚያበረታ ነው፡፡ በእግዚአብሔር እጅ ካልተያዙ (በዓለቱ ላይ ካልተመረቱ) የተለያዩ ገፍተው የሚጥሉ ሰልፎች በገጠሙ ጊዜ ጸንቶ መቆም አይቻልም፡፡

እነዚህ ነገሮች የገጠሙዋቸውና መልካም የእምነት ገድል የተጋደሉ ምሳሌዎች በዙሪያችን እንደ ደመና የከበቡን ስላሉ ከእነርሱ መማር ነው፡፡ ከዚህም ሌላ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እየኖሩና የእግዚአብሔርን አሳብ እያገለገሉ ያሉ ቢሆንም የተለያዩ ልብ የሚያደክሙ/ተስፋ ወደ መቁረጥ የሚያደርሱ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነርሱም

1. **የውጊያ መበርታትና ተከታታይነት**፡- ከኃጢአተኞች የሚደርስ በተለያየ መልኩ የሚገለጽ ውጊያ/ተቃውሞ መበርታትና ተከታታይነት፡፡ ተከታታይ የማያባራ ውጊያ ጀግናው የእግዚአብሔር አሳብ አገልጋይ ንጉስ ዳዊትን እንኳ እንዲህ ዓይነት ቃል ወደ መናገር አድርሶታል፡፡ ጥቅሶቹን ያንብቡ፤ 1ሳሙ 20፡3፣ 1ሳሙ20፡30-31፤ 27፡1፤ ሙሴ፣ ዘሁ11፡10-15፣ ሙሴ እግዚአብሔር የሰጠውን ተግባር ሲፈጽም ብዙ መልካም ውጤት ቢያይም ሕዝቡ በእርሱ ላይ ደጋግመው በቁጣ ስለ ተነሱበት ተስፋ የመቁረጥ ቃል ተናግሯል፡፡
   **ለዚህ ተገቢው መፍትሄ**… ዕብ 12፡3 ጌታ ኢየሱስ ከኃጢአተኞች የደረሰበት ተቃውሞ መታገሱና በጀመረው ጉዞ ንቅንቅ ሳይል የመጽናቱን ምሳሌነት መከተል ነው፡፡ (ፊሊጵ 1፡20-21፣ ሐሥ 4፡19-20፣)
2. **ውጤትን ማየት**፡- በየዕለቱ ለኑሮ በሚከናወን ስራና በመንፈሳዊ አገልግሎት እየተጉና እየደከሙ ይሆናል ብለው ከጠበቁት መልካም ውጤት ለረጅም ጊዜ ተቃራኒው ሆኖ መገኘት፡፡ እኛ ሁል ጊዜ ማለት ይቻላል፣ በምንሰራው ሥራ የምንጠብቀው መልካም ውጤት ብቻ ነው፡፡ እንደ ጠበቅነው ሳይሆን ሲቀር ለምን በአገልግሎቴ/በስራዬ መልካም ውጤት/ስኬት አላየሁም በማለት አለማጉረምረም፣ አለማኩረፍ፡- ተገልጋዩ ህዝብ ቶሎ በፈለግሁት ልክ አልተለወጠም/በእግዚአብሔር ቤት አልጸናም፣ ብዛቱ አላደገም፣ ወንጌል የመሰከርኩለት አልዳነም፣ በአገልግሎቴ ድንቅና ታምራት አልሆነም …ወዘተ አለማለት፡፡
   ኤልያስ፣ 1ነገ19፡4፣ ዮናስ፣ 4፡1-4-8፣

**ተገቢው መፍትሄ፡-- ሀ**) ዮሐ 17፡4 እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤ የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት ያለበት በተሰጠው ጸጋ/ኃላፊነት ለሰው ፊት ሳያዳላ ሁሉን በእኩልነትና በትጋት እስከ ፍጻሜው አገልግያለሁን/ የተሰጠኝን ኃላፊነት ተወጥቻለሁን ማለት ነው፡፡ ነብዩ ኤርምያስ አምላኩ አድርግ ያለውን ያደረገ ቢሆንም፡ በአገልግሎቱ የሰሚዎቹ ሰዎች ሕይወት ግን ተለውጦ አናይም፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ማገልገል የሚገባው በእርሱ ያለንን እምነትና ለእርሱ ያለን

ፍቅር ለመግለጥ ነው እንጂ መልካም ውጤት አስፈላጊ ቢሆንም በዚያ ላይ ማትኮር አይገባም፡፡ የታዘዙትን በማድረግ ውጤቱን ለእግዚአብሔር መተው ነው፡፡

እግዚአብሔር ዋጋ የሚከፍለው/የሚመዝነው እንደ ሰሩት ሥራ ነው እንጂ በሰሩት ሥራ እንዳገኙት ውጤት አይደለም፡፡ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ውጤታማ እንደ ሚያደርገው በመተማመን እርሱ የሰጠውን ኃላፊነት መወጣት ነው፡፡ (ዮሐ 4፡34-38፣)

ለ) በአኗኗሬ ያወቅሁትን የእግዚአብሔርን ቃል በመተግበር የባሕርይ ለውጥ እያሳየሁ ነው ወይ፡ -

- አገልግሎት አሰጣጤ/የተሰጠኝ ኃላፊነት መወጣቴ በእምነት፣ በል-በሙሉነት፣ በፍቅርና በትጋት ያለማቋረጥ በመጽናት ነው ወይ ማለት፤
- የሌላ ሰው ምድራዊ ኑሮ ስኬት ከራስ ኑሮ ጋር አለማስተያየት፣

(ሉቃ 12፡42-48፤ ማቴ 25፡1-15፤ መዝ 37፡34፤ ሰቆ ኤር 3፡24-26፤ ዕብ 3፡14) በሰሩት ስራ ውጤታማ መሆን መልካም ቢሆንም ውጤታማ ባልሆነ አሰልቺ ስራም ጌታ በሰጠው ኃላፊነት ታማኝ ሆኖ መቀጠል እግዚአብሔር ይፈልገዋል፡፡ አድርጉ ያለውን በማድረግ እስከ መጨረሻው ድረስ መሄድ ተገቢ ነው፡፡ ማቴ 25፡21፣ 23፤

3. **የሰውን ሁኔታ ማየት፡-** አብሮ የሚያገለግልም ሆነ የሚገለገል ሰው እንዴት ለመንፈሳዊ ነገር ተዘናግቶ እንደሚኖርና፣ የሰውን (የተገልጋዩን) መልካም የሆነውን እንጂ ክፉ ምላሽ ማየት አይገባም፣ ዮሐ 8፡29፣ የላከኝ እርሱ ከኔ ጋር ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሁል ጊዜ የላከኝ ደስ የሚያሰኘውን ስለማደርግ ብቻዬን አልተወኝም እንዳለው **እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት** የሚሮጡትን አይተዋቸውም፤

- **ተገቢ ምላሽ፡-** በሩጫ ሜዳ ለውድድር የገባ ሰው ሌላው ሯጭ በአግባቡ ቢሮጥም ባይሮጥም በሙሉ ኃይሉ ሽልማት ለማግኘት ይሮጣል፡፡ ዕብ 12፡2 በዚህ ረገድ ፍጹም መልካም ምሳሌያችን የሆነው ጌታ ኢየሱስን ማየት፡፡ ማለትም እርሱ እንዳደረገው በትዕግስት፣ በእምነት፣ በፍቅር፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ በቁርጠኝነት፣ በጽናት የተዘጋጀለንን ከፊታችን ያለውን ሩጫ እእስከ ፍጻሜው መሮጥ ነው፡፡ ዳን 12፡2-3 (ደግሞም ዕብ 11 ላይ የተጠቀሱት በተለያየ ውጣ ውረድ ያለፉ የእምነት አባቶች ማየት)
- አገልግሎትህን ሊያግዝ፣ ስለ ትጋትህ ሊያመሰግን፣ ሊያበረታታ ራሱም በሙሉ ኃይሉ ሊተጋ ሲገባው በተቃራኒው አገልግሎትህን ለማደናቀፍ፣ ሲነቅፍና ሲዋጋ ብታገኘው፣ እርሱ ወይ ገና አልገባውም አለያም የጠላት መጠቀሚያ እየሆነ ሊሆን ስለሚችል አንተ የአምላክህን ፍቅርና ውለታ ነው ማየት ያለብህ፡፡ቆላ 3፡23፣ ዮሐ 14፡15፣

እግዚአብሔር በኛ ሕይወት ማየት የሚፈልገው መልካም ፍሬ ለማፍራት እና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች የሰጠንን ሁሉ ስራ በመስራት ከፍጻሜው ለማድረስ የተቻለንን ሁሉ ጥረት የማድረጋችን ዋና ምክንያቶች መሆን ያለበት፡-

- እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በሰራልን ስራ ስናፍርበት የነበረው ኃጢአታችን ሁሉ ይቅር ስላለን/ምህረት ስላደረገልን፣
- ከጠላቶቻችን ሁሉ ስላዳነን ታላቅ ማዳን፡፡
- በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን የሰጠንን ስራ ሰርተን በመጨረስ ልናከብረው/ደስ ልናሰኘው ስለሚገባን፡፡
- የተዘጋጀልን ከፊታችን ያለው የምንወርሰው ታላቅ ደስታ ለማየት በመናፈቅ መሆን አለበት፡፡ ዕብ 12፡2

4. **የሰው ጊዜ ከእግዚአብሔር ጊዜ ጋር አለመጣጣም** (የጸሎትም መልስም ሆነ የተሰጠ የተስፋ ቃል፣ መፈጸሙ ላይ ሰው በጠበቀው ጊዜ አለመሆን፡፡
ምሳ13፡12 "የምትዘገይ ተስፋ ልብን ታዝላለች፤ የተገኘች ፈቃድ (የተሳካ ምኞት) ግን የሕይወት ዛፍ ናት"
   - አብርሐም ልጅ ትወልዳለህ ከተባለ በኋላ የልጅ መቀበያ ጊዜ ቢዘገይም፣ የሳራም የሴት ወግ የተቋረጠ፣ ሁለቱም ባልና ሚስት በዕድሜ የገፉ፣ ሳራም የተስፋ ቃል ከመሰጠቱም በፊት መካን የነበረች ቢሆንም በእምነቱ አልደከመም፡፡ በእምነት ጠብቆ የተሰጠውን ተስፋ ተቀበለ፡፡ በእምነቱ በመጽናት ለእግዚአብሔር ክብር ሰጠ እንጂ ተስፋ የሰጠውን አልተጠራጠረም፡፡ ልጅ ከወለዱም በኋላ ይስሀቅን ሰዋልኝ ሲለው ሳያንገራግር እሺ እሰዋዋለሁ፣ ቢሞትም ያስነሳዋል ብሎ አመነ፡፡
   - የተስፋ ቃሉ ከእግዚአብሔር መሆኑ ማረጋገጥና እኛም አኗኗራችን በፅድቅ ሕይወትና በእምነት መጠበቅ ላይ እንሁን እንጂ እግዚአብሔር ቃሉን ለመፈጸም ፍጹም ታማኝ ስለሆነ ከቶ አይዋሽም፡፡ ዕንባቆ 2፡1-3፣ ዕብ 6፡17-19፣ ሮሜ 4፡20
   - የተስፋ ቃሉ ባይፈጸምም ከሰጠው ተስፋ ቃሉ የሚበልጠው እግዚአብሔር ለኛ ከሁሉ በላይ ስለሆነ እርሱ እስካለን ድረስ ከሁሉም በላይ በሆነው በእርሱ ደስ መሰኘት ነው፡፡
   - በዚህ ሁኔታ በእምነት ለምትጠባበቁ እግዚአብሔር ተናግሯችሁ የዘገየ ነገር ቢኖር ዛሬ ሊፈጸም መንሳቀስ ይጀምራል፡፡

5. **የእግዚአብሔር ማንነትና አሰራር ዕውቀት ማነስ ወይም ሰው በጠበቀው መንገድና ሁኔታ አለመሆን፡፡** እግዚአብሔር ከኛ ጋር ሆኖ በስራ ላይ እያለ አብሮነቱን መረዳት የሚያቅተን ጊዜ አለ፡፡ እርሱ እኛ በጠበቅነው መንገድ ባይሰራም ምን ጊዜም በስራ ላይ ነው፤ ደግሞም ከኛ ጋር መሆኑን እንዘንጋ፡፡ ማቴ 28፡19-20፣
ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች፡-
ማቴ 11፡2-3……………….. 11፡4-6 ጌታ ኢየሱስና መጥምቁ ዮሐንስ፣
ዮሐ 21፡1-3……………… 21፡4-9 ጌታ ኢየሱስና ዓሳ ሊጠምዱ የሄዱ ደቀመዛሙርት፣
ሉቃ 24፡13-17-21 ……….. 24፡30-43፣ ጌታ ኢየሱስና የኤማሁስ መንገደኞች፣

ኢሳ 55፥8-9 ሀሳቤ እንደ ሀሳባችሁ መንገዴ እንደመንገዳችሁ አይደለም… ሰማያት ከምድር ከፍ እንደሚሉ እንዲሁ ከፍ ያለ ነው፡፡

እግዚአብሔር ታላቅነቱም ሆነ አሰራሩ ከኛ መረዳት እጅግ የላቀ ስለሆነ እግዚአብሔር የተወን፣ ስንቸገር ግድ የማይለው፣ የተናገረው ቃል የማይጠብቅ፣ እርሱ በኛ ላይ ክፉ የሚያደርግበት ጊዜ ያለ ሊመስለን ይችል ይሆናል፡፡

አካሄዳችን ከእግዘዚአብሔር ጋር አድርገናል፣ ከእርሱ ጋር ህብረታችን ያማረ ነው በምንልበት ሰዐት እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ነገር እንዲደርስብን ይፈቅዳል የማንለው ችግር/ውጊያ ሲደርስብን ምንድነው እየሆነ ያለው? ያሰኘናል፡፡

እንዲህ ሁኔታዎች ግራ በሚያጋቡ ጊዜ ይስሀቅ ከአባቱ አብርሐም ጋር ለእግዚአብሔር መስዋዕት ለማቅረብ ሲሄድ የሚሰዋ በግ ሳይዙ እየተጓዙ በመሆናቸው ጥያቄ ቢፈጥርበትም፣ አባቱም ለዚህ ጉዳይ የሰጠው መልስም ያረካው ባይመስልም ዝም ብሎ አባቱን ተከትሎ ሄደ፡፡ ሲመለሱም አባቱ ለምን መሰዊያ ላይ እንዳጋደመው ቢያውቅም እንደ እርሱ የሚሆንለት ማንም ስለሌለ ያው አባቱን ተከትሎ እቤቱ ደረሰ፡፡ ስለዚህ ያልገቡን ነገሮች ሲኖሩ እንደ እግዚአብሔር የሚሆንልን ማንም ስለሌለ እርሱን መከተላችንን አጽንተን በመያዝ መቀጠል ነው፡፡ ምክንያቱም እርሱ አይሳሳትም ፍርድም አያጣምም፡፡
ዘዳ 32፥4፣ ኢዮ 32፥4፣ መዝ 145፥17

ኢዮብ እግዚአብሔር ራሱ ጻድቅነቱ የመሰከረለት ሆኖ ሳለ በጣም ከባድ ፈተና ስለደረሰበት በአምላኩ ላይ አጉረምርሟል፡ በኋላ አምላኩ ለኢዮብ ሲመልስለት 4 ጊዜ (ኢዮ 38፥2፣ 34፥ 35፣ 35፥16፣ 36፥12) የኢዮብ ንግግር ዕውቀት/ማስተዋልና ጥበብ የጎደለው ነው ብሎታል፡፡

አዮብም ራሱ መልሶ እግዚአብሔር ሲናገረው ነቅቶ (ኢዮ 42፥3) አዎን የማላውቀውና ላስተውለው የማልችለውን ነገር ተናግሬያለሁ በማለት መሳሳቱን አምኗል፡፡

ኢዮብ በምስራቅ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ባለጠጋ ስለነበር የእርሱ ሁኔታ የብልጥግና የመጨረሻ ጣሪያ ተደርጎ ከመታወቅ በቀር እግዚአብሔር ከዚያ በላይ ያበለጽገዋል ብሎ የሚያስብ ራሱም ሆነ ሌላ ሰው ላይኖር ይችላል፡፡ ከፈተናው በፊት አምላኩ ጥበቃ ያደርግለትና የእጁን ስራ ይባርክ ነበር፡፡ ከመከራው በኋላ ለሰውነቱ ሙሉ ፈውስ በማድረግ፣ በንብረትም ከቀድሞው እጥፍ በመባረክ የላቀ ነገር መስራት የሚችል መሆኑን አሳየው፡፡ አዮ 42፥10፣ 12፡፡ የኢዮብ አምላክ የኛም አምላክ ስለሆነ በፊቱ በቅንነት የምትመላለሱ በእውቀት ማነስ በእግዚአብሔር ላይ ስለተናገራችሁት ቃል ንስህ ግቡ፡፡ ዛሬ የተያዘባችሁ ሙሉ ጤንነት ይለቀቃል፡፡ የተወሰደባችሁ መንፈሳዊም ሆነ ምድራዊ በረከት ምርኮ ብዙ እጥፍ አድርጎ መመለስ ይችላል፡፡

ጌታ ኢየሱስ የማርያምና ማርታ ወንድም መሞት "የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ… ነው እንጂ ለሞት የሚያደርስ አይደለም" አለ፡፡ አንዳንዶች ይህን ዐረፍተ ነገር፣ እግዚአብሔር ለስሙ ክብር ሲል የማርያምና ማርታን ቤት ይህን ያህል ማስጨነቁ ተገቢ

ነውን? ይላሉ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክብሩን የሚገልጥበት አንዱ ምክንያት፣ ዓይተነው የማናውቀው ታላቅ ተዓምራዊ ስራ ሰርቶ በማሳየት ይበልጥ እንድንተማመንበት ነው፡፡ ስለዚህ ታምራዊ ስራ የሚሰራው ሕዝቡን ለመጥቀም ነው እንጂ ለማስጨነቅ አይደለም፡፡ ማርያምና ማርታን ጨምሮ ሌሎች አይሁዶችም ጌታን ያውቁት የነበረው የታመመን መፈወስ እንደሚችል ብቻ ነበር፡፡

ዮሐ 11፡3፣4፣ 21-25፣ 32፣ 35-37፣ 39-41፤ እነዚህ ጥቅሶች የሚሉትን ስንመለከት፡-

ኢየሱስ ግን ወንድምሽ ይነሳል አላት፡፡ አሁንም ስላልተግባቡ በተጨማሪ ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ አላት፡፡ ማርታ ትንሳኤና ሕይወት አርሱ መሆኑን ስላላወቀች አጠገቧ እያለ ወንድሜ ስለሞተ የርሱ ነገር አብቅቷል በመጨረሻው ቀን በሙታን ትንሳኤ ጊዜ ይነሳል አለች፡፡ መቃብሩ ጋ ደርሰው የተገጠመው ድንጋይ አንሱ ሲል ማርታ መነሳት የለበትም አሁንማ በስብሶ ይሸታል ብላ ተከራከረችው፡፡ ጌታ ግን ሞቶ የተቀበረው ወንድሚን አስነስቶ በሕይወት በማኖር ታላቅ ኃይሉና ችሎታው አሳያት፡፡ ትንሳኤና ህይወት የሚሰጥ የእግዚአብሔር መንፈስ አጠገባችን ሁል ጊዜ እንዳለ የምታምኑ የሞተ ያህል የሆነባችሁ ነገር ሁሉ ያስነሳዋል፡፡

ከዚህ በፊት አስበውትም ሆነ አይተውት የማያውቁት የጌታ ኢየሱስ ክብር/ታላቅ ችሎታና ኃይል ባደረገው ተዓምራዊ ሥራ ምክንያት ቀድሞ ያውቁት ከነበረው በላይ ታላቅ መሆኑን እንዲያውቁት በማድረጉ እነርሱ ናቸው ተጠቃሚዎች የሚሆኑት፡፡ ስለዚህ ከዚያ ጊዜ በኋላ በእግዚአብሔር ያላቸው መተማመንና ለእርሱ መገዛታቸው ያድጋል፡፡ ይህ በተራው ሌላ ያላዩት የእግዚአብሔር ታላቅነት ክብር ማየት ያስችላቸዋል፣ የበለጠ ተጠቃሚዎች ያደርጋቸዋል፡፡

ክርስቲያኖች ፈተናን/መከራን ሊያዩት የሚገባው ከኃጢአት መመለሻ ቅጣት፣ በጠላቶቻችን ላይ እንድንበረታ ማሰልጠኛ (ሰልፍ/ውጊያ ማስተማሪያ;) ከክብር ወደ ላቀ ክብር ማድረሻ መሰላል በመሆኑ እንደ መልካም ዕድል ነው መታየት ያለበት፡፡ በእምነት ውጊያ ድል ማጣጣም ለለመዱት ልዩ ልዩ ፈተና ወደ ከፍታ መውጫ መሰላል ነው፡፡ ጎልያድና ንጉስ ሳኦል ያዩት ሥጋዊ የጡንቻ ብርታትና በስጋዊ የጦርነት ልምምድ ሲሆን፣ በ1ሳሙ 17፡33-37፣ ዳዊት ለሳኦል እንደተናገረው፡፡ ዳዊት ያየው ግን የራሱን አካላዊ ብቃት ሳይሆን የአምላኩ ታላቅነትና የእምነት ውጊያ ልምምዱን ነው፡፡

ዕለት ተዕለት ከእግዚአብሔር ጋር በህብረት ለመጓዝ የጀመሩት ጉዞ ለማደናቀፍ ከዓለም በሚሰጥ አጸፋዊ ምላሽ ሳይደናገጡ ጉዞን በትዕግስት፤ በእግዚአብሔር መታመንን ላፍታ ባለማቋረጥ የገጠመ ችግርን በጸሎት በፊቱ በማቅረብ፤ ስለ ሁሉ በማመስገንና በእርሱ ደስ በመሰኘት በላይ ያለውን ዋነኛ ራዕያችንና ተስፋችንን በማሰብ መጽናት ይሁንልን፡፡ አሜን?!!

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)                2018 ዓ.ም.